Seattle

# የWest Seattle እና የBallard ቀላል ባቡር ማስፋፊያ

# የተገናኙ ማህበረሰቦችን መፍጠር

የLink Light Rail በሲያትል እየተስፋፋ ነው!

Sound Transit በ2032 ወደ West Seattle እና Ballard በ2037-2039 13 አዳዲስ እና የተስፋፉ የቀላል ባቡር ጣቢያዎችን ከአገልግሎት ጋር እየገነባ ነው። ይህ በSeattle ውስጥ ያለው የቀላል ባቡር መስፋፋት በመሃል ከተማ ስር አዲስ የሕዝብ ማመላለሻ መሿለኪያ እና ሁለት የውሃ ማቋረጫዎችን ያካትታል። በከተማችን ታሪክ ውስጥ ይህ እጅግ ትልቁ የሕዝብ መጓጓዣ መዋዕለ ንዋይ ነው።

ከተማዋ በአጎራባቾች እና በስራ ማዕከላት መካከል ፈጣን እና አስተማማኝ የሕዝብ መጓጓዣ ግንኙነቶችን ለማረጋገጥ እና እንዲሁም ሰፈሮችንን ለማሻሻል የበለጠ አካታች፣ ተመጣጣኝ ዋጋ፣ እና እርስ በርስ ትስስር ያላቸው መዳረሻዎች እንዲሆኑ ለማድረግ አዲስ የቀላል ባቡር ለመስራት እያቀደ ነው።

*የፕሮጀክት ማስረከቢያው ቀናትን በተመለከተ ዝርዝሮችን ለማግኘት፣ እባክዎ የSound Transit




## አብረን እናቅድ

- የዘር እኩልነት እና ማህበራዊ ፍትህ በቀላል ባቡር ጣቢያዎች እና አሰላለፍ ላይ የከተማ ውሳኔ አሰጣጥ መሰረት ናቸው።
- ወደ ሰፈራችሁ የሚመጣ አዲስ የቀላል ባቡር አገልግሎት፣ ወደሚፈልጉበት ቦታ ለመሄድ አንድ ቀልጣፋ እና አስተማማኝ አማራጭ ይሰጥዎታል።
- በጣቢያዎች አቅራቢያ የሚገኙ አዳዲስ ተመጣጣኝ መኖሪያ ቤቶች እና ንግዶች የተለያዩ የመኖሪያ አካባቢዎችን የበለጠ የመኖሪያ፣ የመስሪያ እና የመገበያያ ቦታዎችን ሊያሳድጉ ይችላሉ።
- በመኪናዎች ላይ ያለንን ጥገኝነት በመቀነስ እና ለነዋሪዎች እውነተኛ፣ እና ለመጓጓዣ ንጹህ የሃይል አማራጮች መስጠት የአየር ንብረት ለውጥን እንደገና ለመቋቋም እንድንታገል ይረዳናል።

**የSeattle ከተማ እና የSound Transit በዚህ ሂደት ውስጥ ሁሉ ማህበረሰቦችን ለማሳተፍ አብረው በጋራ እየሰሩ ናቸው። ይህን ፕሮጀክት ለማህበረሰብ ፍላጎቶች እና ምኞቶች ምላሽ በሚሰጡ መንገዶች በጊዜ፣ በበጀት፣ እንዲደርስ ከማህበረሰቦች ጋር በመገናኘት ውስጥ እያንዳንዱ ሽሪክ ሚና ይጫወታል።**

### City of Seattle ሚና

- ከንቲባ Bruce Harrell እና የምክር ቤት አባል Debora Juarez የመጨረሻ ውሳኔዎችን በሚያደርጉት በSound Transit ቦርድ ላይ ይቀመጣሉ።
- በአዳዲስ ጣቢያዎች ዙሪያ ያሉ ምርጥ ተጐራባቾችን ለማሻሻል መኖሪያ ቤትን፣ ንግዶችን እና ክፍት ቦታዎችን ያቅዳሉ።
- ጣቢያዎችን እና ዝርጊያዎችን ለመስራት ለSound Transit ፈቃዶችን ይሰጣሉ።

### SoundTransit ሚና

- ሊሆኑ የሚችሉ አሰላለፍ እና የጣቢያ ቦታዎችን ይገመግማሉ።
- የቀላል ባቡር ስርዓት ቅድመ እቅድ፣ የአካባቢ ግምገማ እና ቅየሳ።
- አዲስ የቀላል ባቡር ስርዓትን ይገነባሉ እና ያካሄዳሉ።

**የበለጠ በ Seattle.gov/lightrail ላይ ይረዱ**



# የጊዜ ሰሌዳ

**ቀጣይነት ያለው የማህበረሰብ ተሳትፎ**

| ሐምሌ 2022 | ከረፋዱ 2022 - 2023 አጋማሽ | የካቲት 2023 | በ2023 መጨረሻ - 2024 መጀመሪያ | በ2024 መጀመሪያ |
|---|---|---|---|---|
| የSound Transit ቦርድ ለWest Seattle Link ተመራጭ አማራጭ ተለይቶ እንዲታወቅ አድርጓል፣ ለBallard Link አማራጮች ተጨማሪ ጥናት ጠይቋል | የከተማ እና የSound Transit የጣቢያ አውድ እቅድ ማውጣት የህዝብ ተሳትፎ ያካሄዳሉ | የSound Transit ቦርድ የተጠየቀውን ጥናት መገምገም<br>በBallard Link ላይ የቦርድ እርምጃ መወሰን | የመጨረሻ የተፈጥሮአዊ-አካባቢ ተፅእኖ መግለጫ (FEIS) ይታተማል | የመጨረሻ መስመር አሰላለፍ እና የጣቢያ ቦታዎች<br>በSound Transit ቦርድ, በፌደራል የሕዝብ መጓጓዣ አስተዳደር, እና በSeattle ከተማ ምክር ቤት ተረጋግጠዋል |

## በጣቢያዎች ዙሪያ ማቀድ

በ2024 መጀመሪያ ላይ Sound Transit የመጨረሻውን የቀላል ባቡር ጣቢያ ቦታዎችን በመለየት ካወቀ በኋላ፣ የSeattle ከተማ የጣቢያ አካባቢ የማቀድ ሂደቱን ይጀምራል እና ከማህበረሰቦች ጋር የሚከተሉትን ለማድረግ ይሰራል:

- እርስዎ ወደ ጣቢያዎች እንዲደርሱዎት ለመርዳት የእግር መሄጃውን፣ የብስክሌት መጋለብን፣ እና የአውቶቡስ ማሻሻያዎችን ማቀድ።
- በአዳዲስ ጣቢያዎች ዙሪያ የዋጋ ተመጣጣኝነት ያለው፣ ለኑሮ ምቹ የሆኑ ሰፈሮችን ለመፍጠር የመኖሪያ፣ የመገበያያ እና ክፍት ቦታዎችን እድሎችን ለይቶ ማወቅ።
- ፕሮጀክት መፍቀድን ለማሳወቅ ቅድሚያ የሚሰጣቸውን ነገሮች መመስረት።

ሰፈሮቻቸው በታሪክ ትልቅ የመዋቅራዊ መሠረተ ልማት ግንባታዎችን ሸክም በጫናቸው የተሸከሙ የቀለም ማህበረሰቦች ላይ ልዩ ትኩረት በማድረግ ከተማዋ የዘር እና የማህበራዊ ፍትህ ተነሳሽነትን (Race and Social Justice Initiative) በዚህ ፕሮጀክት ተግባራዊ ለማድረግ እየሰራች ነው።




የSeattle ከተማ እና የSound Transit እቅድ ለማውጣት በጋራ አብረው እየሰሩ ነው፣ የ**<u>ጣቢያ አውድ</u>** አካባቢ፣ ይህም ከጣቢያው ከአንድ እስከ ሁለት ብሎኮች ውስጥ ያለ አካባቢ ነው። የጣቢያ አውድ እቅድ ማውጣት ለራሱ ለጣቢያው የንድፍ ምርጫዎችን፣ በጣቢያው ዙሪያ ያለውን ክፍት ቦታ፣ የአውቶቡስ ማቆሚያዎችን እና ሌሎችንም ያካትታል።

ከተማው በተለምዶ ከጣቢያው በግማሽ ማይል ርቀት መካከል ያለውን ሰፊውን ቦታ የ**<u>ጣቢያ አካባቢ</u>** እቅድ ለማውጣት ከማህበረሰቦች ጋር የመስራት ሃላፊነት አለበት።

## በተሳትፎ እንደተገኙ ይቆዩ

ስለከተማው መጪ የማህበረሰብ ስብሰባዎች ለማወቅ እና ለዝማኔዎች በ seattle.gov/lightrail **ላይ ይመዝገቡ።**

በSound Transit ላይ የቅርብ ጊዜ ዝመናዎችን ለማግኘት soundtransit.org/wsblink **ይጎብኙ።**

## የSeattle ከተማ መገናኛዎች

**Sara Maxana**
አመራር እና መጓጓዣ
206.233.3369
sara.maxana@seattle.gov

**Vera Giampietro**
ማቀድ እና ንድፍ
206.684.0431
vera.giampietro@seattle.gov

**Nicole Kistler**
ተሳትፎ
206.962.9266
nicole.kistler@seattle.gov

## ለዝማኔዎች በ seattle.gov/lightrail ላይ ይመዝገቡ

የSeattle ከተማ እያንዳንዱ ሰው በከተማዋ ፕሮግራሞች እና በእንቅስቃሴዎቿ ውስጥ እንዲሳተፍ ያበረታታል። ለአካል ጉዳተኝነት መስተናገጃዎች፣ የመረጃ ልዩ ልዩ ማስረጃዎችን በተለዋጭ ቅርፀቶች፣ ወይም የተደራሽነት መረጃን ለማግኘት Nicole Kistlerን | 206.962.9266 | ያነጋግሩ ወይም ባገኙ የመጀመሪያ ዕድል nicole.kistler@seattle.gov በኢሜይል ያግኙ።